በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትሕ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ማ ርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE


ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/........../18

ቀን፡-....../04/2018 ዓ/ም

ለአብክመ ፕላንና ልማት ቢሮ

ባህር ዳር፤

ጉዳዩ፡- መመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው በመላክ እንዲሁም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አዋጁ በወጣ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

በዚህ መሰረት የአብክመ ፕላንና ልማት ቢሮ በቁጥር ፕል/144/32/18 በቀን 14/04/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የፕላንና ልማት ቢሮ የከተማና የገጠር አስተዳደር እርከን ወሰን ለማካለል መመሪያ ቁጥር 4/2018 ዓ.ም ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወሳል፡፡

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮና አስተካክሎ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 21/2018 ዓ.ም አድርጎ የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ 17 ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ገረመው እሸቱ

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት
የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤(ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

ፍትህ ቢሮ

## መመሪያ ቁጥር 21/2018 ዓ/ም

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕላንና ልማት ቢሮ የከተማና የገጠር አስተዳደር እርከን ወሰን ለማካለል የወጣ መመሪያ

የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ የአስተዳደር ወሰን፣ መለያ ኮዶችን በመስጠት የካርታ ሥራ እንዲሠራ፣ የሥነ-ሕዝብ መረጃዎችን እንዲያደራጅ እና ለተጠቃሚዎችም የማሰራጨት ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 300/2017 አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 26 መሠረት የተሰጠው በመሆኑ፤

የከተማም ሆነ የገጠር አስተዳደራዊ መዋቅሮች ቅንጅታዊ አሠራርን የሚያጎለብትና የየራሳቸውን መረጃዎች ወጥ በሆነ መልኩ ለማደራጀት፣ ለመተንተንና ለተጠቃሚ አካላት ለማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕላንና ልማት ቢሮ በአዋጅ ቁጥር 300/2017 አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሰ) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕላንና ልማት ቢሮ የከተማና የገጠር አስተዳደር እርከን ወሰን ለማካለል የወጣ መመሪያ ቁጥር 21/2018 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

1/ **"ምክር ቤት"** ማለት እንደ አግባብነቱ የአማራ ክልል መስተዳድር፣ የብሄረሰብ አስተዳደሮች፣ የከተማ አስተዳደሮች፣ የወረዳ እና ቀበሌ አስተዳደሮች ምክር ቤት ነው፤

2/ **"አግባብ ያለው አካል"** ማለት የአስተዳደር እርከኖችን የሚያቋቁም፣ ወይም በየደረጃው የሚቀርቡ የወሰን ጥያቄዎችን ተቀብሎ ምላሽ የሚሰጥ የክልሉ መንግሥት አካል ነው፤

3/ **"ከንቲባ"** ማለት በከተማው ምክር ቤት አማካኝነት የሚመረጥ ሆኖ የከተማውን ፖለቲካ ፣ አስተዳደር ፣ የልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ስራዎች በበላይነት የሚመራ ዋና ስራ አስፈፃሚ ነው።

4/ **"ከተማ"** ማለት ሁለት ሺህና ከዚያ በላይ የሆነ ህዝብ በአንድ ላይ ተሰባስቦ የሚኖርበትና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በሚያወጣቸው መመዘኛዎች መሠረት ክልሉ "ከተማ" ብሎ የሚሰይመው ማናቸውም አካባቢ ነው፤

5/ **"የከተማ አስተዳደር"** ማለት በክልሉ ውስጥ ተለይቶ በታወቀ መልክዓ-ምድራዊ ወሰን የተደራጀና የአንድን ከተማ ነዋሪ ህዝብ የፖለቲካ፣ የአስተዳደር፣ የልማትና

የአገልግሎት አሰጣጥ ሥልጣንና ኃላፊነቶችን ተረክቦ የሚመራ የአካባቢ አስተዳደር ነው፡፡

6/ **"የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር"** ማለት የአንድን ከተማ ሁለንተናዊ ልማት ከማፋጠን አንፃር ዓይነተኛ ማዕከል በመሆን በዙሪያው የሚገኙትን አነስተኛ ከተሞች ይዞ ወይም አጠቃሎ እንዲያድግ ለተመረጠ ለማናቸውም የክልሉ ከተማ የተሰጠ መጠሪያ ነው፡፡

7/ **"ክፍለ -ከተማ"** ማለት በሪጂዮ -ፖሊታንና እንደ ከተማው የዕድገት ሁኔታ በፈርጅ አንድ ስር በሚጠቃለሉ ከተሞች ውስጥ ከከተማ አስተዳደር ቀጥሎ የሚገኝ የአስተዳደር እርከን ነው፤

8/ **"የዞን አስተዳደር"** ማለት በክልሉ ውስጥ ተለይቶ በታወቀ መልክዓ-ምድራዊ ወሰን የተደራጀና የአንድን ዞን ነዋሪ ህዝብ የፖለቲካ፣ የአስተዳደር፣ የልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥልጣንና ኃላፊነቶችን ተረክቦ የሚመራ የአስተዳደር እርከን ነው፤

9/ **"የወረዳ አስተዳደር"** ማለት በክልሉ በተደራጀ የዞን አስተዳደር ውስጥ ተለይቶ በታወቀ መልክዓ-ምድራዊ ወሰን የተደራጀና የአንድን ወረዳ ነዋሪ ህዝብ የፖለቲካ፣ የአስተዳደር፣ የልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥልጣንና ኃላፊነቶችን ተረክቦ የሚመራ የአስተዳደር እርከን ነው፤

10/ **"ቀበሌ"** ማለት በወረዳ/ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኝ ድንበሩ በግልፅ የሚታወቅና የራሱ ህጋዊ አመራር ያለው የክልሉ ዝቅተኛው አስተዳደር እርከን ነው፤

11/ **"የከተማ ቀበሌ"** ማለት በከተሞች ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ነው፤

12/ **"የገጠር ቀበሌ"** ማለት በወረዳ ውስጥ በገጠር አካባቢ የሚገኝ ዝቅተኛ የአስተዳደር አካል ነው፤

13/ **"በከተማ አስተዳደር የተጠቃለለ የገጠር ቀበሌ"** ማለት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የከተማነት ደረጃ በሰጠው በየትኛውም ከተማ ወሰን የተካተተ ወይም የታቀፈ የገጠር ቀበሌ ነው፤

14/ **"የአስተዳደር እርከን"** ማለት በማናቸውም በከተማ እና በገጠር ውስጥ የህዝብ ብዛትን መሰረት በማድረግ የተዋቀረ የተዋረድ የአስተዳደር ደረጃ ነው፤

15/ **"የከተማ ፕላን"** ማለት ሥልጣን ባለው አካል የፀደቀና ህጋዊ ተፈፃሚነት ያለው የከተማ መዋቅራዊ ፕላን፣ የአካባቢ ልማት ፕላን ወይም መሠረታዊ ፕላን ሲሆን አባሪ የፅሁፍ ማብራሪያዎችን ይጨምራል፤

16/ **"የአስተዳደር ማዕከል"** ማለት ለክልል፣ ለዞን፣ ለወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደሮች አስተዳደራዊ መቀመጫነት የሚያገለግል ከተማ ነው፤

17/ **"የገጠር ማዕከል"** ማለት በጥናት ተደግፎ በነዋሪው ህዝብ አስተያየት አግባብ ባለው የወረዳ አስተዳደር በኩል ለመኖሪያነትም ሆነ ለሌሎች የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አገልግሎቶች የተመረጠ ቦታ ነው፤

18/ **"የቆዳ ስፋት"** ማለት የአስተዳደር እርከኖች በሕግ አግባብ ተለይቶ የሚያስተዳድሩት እና የተከለለ የአስተዳደር ወሰን ያለው በስኩየር ኪሎ ሜትር ወይም በሄክታር የሚገለፅ የአስተዳደር አካባቢ ነው፤

19/ **"የአስተዳደር ወሰን"** ማለት በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና ቀበሌዎች አንዱ ከሌላው ጋር የሚዋሰኑበት ወሰን ነው፤

20/ **"ካርታ"** ማለት መሬት ላይ የሚገኙትን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የሆኑ ገፅታዎችን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል አነስተኛ በሆነ መልኩ እንዲያሳይ አድርጎ በማዘጋጀትና በማስፈር የማሳየት ዘዴ ነው፤

21/ **"የአየር ላይ ራዲዩስ"** ማለት በመስፈርቱና በስታንዳርዱ መሠረት ከአንድ ከተማ ማዕከል ተነስቶ በሚጠይቀው ልኬት መሠረት በአየር ላይ የመለካት ዘዴ ነው፤

22/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው

23/ በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሁሉ የሴትንም ፆታ ይመለከታል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ፦

በክልሉ ውስጥ በተቋቋሙ ወይም በሚቋቋሙ ዞኖች፣ ሪጆ-ፖሊታን ከተሞች፣ የከተማ አስተዳደሮች፣ የገጠር ወረዳዎች እንዲሁም በክልሉ የከተማና የገጠር ቀበሌዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የመመሪያው ዓላማ

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1/ በክልሉ የከተሞች የአስተዳደር ወሰን አከላለል ጋር ተያይዞ የሚታዩ ዋና ዋና ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት፤

2/ ከተሞች የአስተዳደር ወሰኖቻቸውን ለማካለል የሚመለከተው አካል ወቅታዊ፣ ታማኝነቱን የጠበቀና ወጥ የሆነ ግንዛቤና መረጃ በመያዝ የወሰን ማካለል ሥራዎችን እንዲሰራ ለማስቻል፤

3/ ዞኖችን፣ ከተሞችን እና ወረዳዎችን በሚያሳድግ ሁኔታ ለማስተዳደር የሚያስችል አቅም ለመፍጠር፤

4/ በአስተማማኝ መረጃ ላይ በመመስረት የወሰን ይካለልልን ጥያቄዎችን በወቅቱና በጥራት ለማካለል የሚያስችሉ ቅድመ-ሁኔታዎችን በማሟላት ረገድ ኃላፊነት ያለባቸው አካላት ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ስለ ከተሞች፣ የገጠር አስተዳደር ወረዳዎችና ቀበሌዎች ወሰን አከላለል

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ስለከተሞች ወሰን አከላለል

### 5. ስለከተሞች ወሰን

1/ የሪጂዮፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች ወሰን ከማዕከላዊ የከተማው ስፍራ በመነሳት፡-

ሀ) በዙሪያው እስከ 30 ኪ.ሎ ሜትር የአየር ራዲየስ የሚገኘውን መልከዓ-ምድራዊ ክልል እና በውስጡ የሚገኘውን ነዋሪ ሕዝብ፤

ለ) በአማካይ እስከ 30 ኪ.ሎ ሜትር ራዲየስ የሚገኙ ወሰናቸው የተለየ የአካባቢ አስተዳደር አቋም ያላቸው ከተሞችንና በውስጣቸው የሚገኘውን ነዋሪ ሕዝብ ያጠቃልላል፡፡

2/ የመካከለኛ ከተማ አስተዳደር ከተሞች ወሰን ከየከተሞቹ ማዕከላዊ ስፍራ በመነሳት በዙሪያቸው እንደ ሁኔታው 15 ኪሎ ሜትር የአየር ርቀት ራዲየስ ዙሪያ ያለውን መልከዓ-ምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚኖሩ ህዝቦችን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

3/ የአነስተኛ ከተማ አስተዳደር ከተሞች ወሰን ከየከተሞቹ ማዕከላዊ ስፍራ በመነሳት በዙሪያቸው እንደ ሁኔታው 5 ኪሎ ሜትር የአየር ርቀት ራዲየስ ዙሪያ ያለውን መልከዓ-ምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚኖሩ ሕዝቦችን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

## 6. ስለ ከተሞች ወሰን አከላለል

1/ የከተማ ወሰን ሲካለል የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡-

ሀ) የከተማ ወሰን እንዲካለልለት የጠየቀው ከተማ ወይም የገጠር ቀበሌ የወሰን ማካለሉ ሥራ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው አግባብ ባለው አካል መወሰኑ የተረጋገጠ መሆኑን፣

ለ) አግባብ ባለው አካል የተሰጠው ውሳኔ ቃለ-ጉባኤ ጉዳዩ በተጀመረ በሁለት ወር ውስጥ አሟልተው ለክልሉ ፕላን እና ልማት ቢሮ ያደረሱ መሆኑን፤

2/ በከተማ እድገት ምክንያት ከአዋሳኝ ወረዳዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 በተገለፀው ርቀት ውስጥ የሚገኙትን ቀበሌዎችን ማካተት ይቻላል፤ ሆኖም በማናቸውም ምክንያት በቅርበት የሚገኙ አዋሳኝ ቀበሌዎችን በመዝለል ሌሎችን ማካተትና ማካለል አይቻልም፤

3/ ከተሞች አጎራባች ቀበሌዎችን በማካተት የአስተዳደራዊ ወሰናቸውን ለማሳደግ ጠይቀው አግባብ ባለው አካል ተቀባይነት ማግኘታቸው ከተረጋገጠ ወደ ከተማዎቹ የሚካተቱት ቀበሌዎችና ሲያስተዳድሯቸው የነበሩት ወረዳ አስተዳደሮች ወደ ከተሞች የመካተት ሂደቱን ተቀብለው ጉዳዩ በተጀመረ በሦስት ወራት ውስጥ ወደ ከተሞቹ እንዲካተቱ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፤

4/ አነስተኛ ከተሞች በአየር ላይ 5 ኪሎሜትር ራዲየስ ድረስ ማጠቃለልና ማካለል ይችላሉ፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመላከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በ5 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ውስጥ ሆነው ወደ ከተማ ያልተካተቱ ነገር ግን ወደ ከተማ አስተዳደሩ የመግባት ፍላጎት ያላቸው አካባቢዎችን በወረዳ መስተዳድር ምክር ቤቶች በማስወሰን ወደ ከተማ አስተዳደሩ አካቶ የማካለል ሥራው የሚሠራ ይሆናል፤

6/ ማንኛውም ከተማ እያደገ በመምጣቱ ምክንያት ወደ ከተማ የመካተት ጥያቄ ቀርቦ አግባብ ያለው አካል ሲወስን በአዋሳኝ የሚገኙ ቀበሌዎችን በዚህ መመሪያ መሠረት የማካለል መብት ይኖረዋል፤

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት በተደረገ የማካለል ሂደት ወደ ከተማ ሳይካተቱ የቀሩ ቀበሌዎች ቢኖሩ የቀበሌዎች ቁጥር አንድ ወረዳ በሕግ ሊኖረው ከሚገባው ቀበሌዎች ቁጥር ያነሰ በሚሆንበት ጊዜ የሚመለከታቸውን አካላት በማማከር እና የነዋሪዎቹን ፍላጎት በማጥናት አግባብ ባለው አካል ሲወሰን ወደ አቅራቢያቸው ወረዳ/ከተማ በማጠቃለል የወሰን ማካለል ሥራው ይከናወናል፤

8/ የገጠር ቀበሌዎች ወደ ከተማ አስተዳደር ወሰን ሲጠቃለሉ ቀበሌዎቹን የሚረከበው ከተማ አስተዳደር ለሚረከባቸው የእነዚህ ቀበሌ ነዋሪ ሕዝቦች ማንኛውንም ዐይነት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተቋማትን ማቋቋምና ማደራጀት ይጠበቅበታል፤

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት የተመላከቱትን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን በአንድ ዓመት ጊዜ ማቋቋም እና አገልግሎቱን መስጠት አለበት፤

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማቋቋም እና አገልግሎቱን መስጠት ባይችል እነዚህ ቀበሌዎች በጀታቸውን ይዘው ቀድሞ ከነበሩበት ወረዳ አስፈላጊውን አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው፤

11/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 10 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀበሌዎቹን የተረከበው ከተማ አስተዳደር ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ ቢበዛ በሁለት ዓመታት ውስጥ ማንኛውንም አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን አቋቁሞና አደራጅቶ ለተረከባቸው ቀበሌዎች አስፈላጊውን አገልግሎትና አቅርቦት የማሟላት ግዴታ አለበት፤

12/ የከተማ ፕላን ሲዘጋጅ የከተማውን የመልማት አቅም ታይቶ በሚዘጋጀው ካርታ መሰረት መሆን አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የገጠር አስተዳደራዊ እርከኖች ወሰንን ስለ ማካለል

### 7. የገጠር አስተዳደር ወረዳዎች እና ቀበሌዎች አስተዳደራዊ ወሰንን ማካለል

1/ በገጠሩ አካባቢ ተለይቶ ለተቋቋመ የአስተዳደራዊ እርከን የክልሉ ፕላን እና ልማት ቢሮ ወሰኑን በማካለል የካርታ መለያ ኮዶችን በመስጠት መረጃዎችን በተደራጀ መልኩ ይሰራል፡፡

2/ በክልሉ የገጠር አስተዳደር እርከኖች ተጎራባች አስተዳደሮች የድንበር አለመግባባት ሲኖራቸው ችግሩ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ስር በተቋቋመው ኮሚቴ እልባትና ዘለቄታዊ መፍትሄ ከተሰጠው በኋላ የክልሉ ፕላን እና ልማት ቢሮ ወሰኖችን የማካለል ስራዎች ይሰራል፤

3/ በአንድ ወረዳ ውስጥ ሊካተቱ ሲገባቸው በተለያየ ምክንያት በጎረቤት ወረዳ አስተዳደር ስር የሆኑ የገጠር ቀበሌዎች ሲያጋጥሙ አግባብ ላለው አካል አቅርበው ውሳኔ ሲሰጥ የክልሉ ፕላን እና ልማት ቢሮ ወሰኖቻቸውን በመለየት እና የካርታ መለያ ኮዶችን በመስጠት ካርታቸውን የማዘጋጀት ሥራ ይሰራል፤

4/ በክልሉ የገጠር የአስተዳደር እርከኖች የስያሜ ለውጥ ሲደረግ የክልሉ ፕላን እና ልማት ቢሮ ወሰኖቻቸውን እና መለያ ኮዶችን በማረጋገጥ የካርታ ሥራ ይሠራል፤

5/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆኖ በማናቸውም ጊዜ በዞኖች፣ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች የአስተዳደር እርከን በኩል የሚነሱ የወሰን ጥያቄዎችን በማጥናት በሚደረስበት ስምምነት መሠረት የክልሉ ፕላን እና ልማት ቢሮ የወሰን ማካለል ስራዎችን ይሰራል፤

6/ አንድ የገጠር ቀበሌ ወደ ሌላ የገጠር ወረዳ አስተዳደር ወሰን ሲጠቃለል ቀበሌውን የሚረከበው ወረዳ አስተዳደር ለሚረከበው ቀበሌ ነዋሪ ሕዝቦች ማንኛውንም ዐይነት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተቋማትን ማቋቋምና ማደራጀት ይጠበቅበታል፤

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት የተመላከቱትን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን በአንድ ዓመት ጊዜ ማቋቋም እና አገልግሎቱን መስጠት አለበት፤

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማቋቋም እና አገልግሎቱን መስጠት ባይችል እነዚህ ቀበሌዎች በጀታቸውን ይዘው ቀድሞ ከነበሩበት ወረዳ አስፈላጊውን አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው፤

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀበሌዎቹን የተረከበው የገጠር ወረዳ አስተዳደር ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ ቢበዛ በሁለት ዓመታት ውስጥ ማንኛውንም አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን አቋቁሞና አደራጅቶ ለተረከባቸው ቀበሌዎች አስፈላጊውን አገልግሎትና አቅርቦት የማሟላት ግዴታ አለበት።

## 8. የቀበሌ አስተዳደር ወሰን ስለሚከለልበት ሥርዓት

የማንኛውም ከተማ ወይም የገጠር ቀበሌ ወሰኑ ሊከለል የሚችለው አግባብ ያለው አካል ወስኖ በቀበሌነት ሲያቋቁመው ብቻ ነው።

## 9. የቀበሌ ስም ለውጥ ስለማድረግ

1/ የከተማም ሆነ የገጠር ቀበሌ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የስም ለውጥ እንዲደረግለት መጠየቅ ይችላል፤

2/ የአንድን ቀበሌ ስም ለውጥ ማድረግ የሚቻለው፦

ሀ) በቀበሌው ነዋሪዎች የተደረሰው ስምምነት በቀበሌ ምክር ቤት፣

ለ) ቀበሌው ተጠሪ በሆነለት የአስተዳደር እርከን ወይም መስተዳድር ምክር ቤት ተቀባይነት ሲያገኝ ነው።

# ክፍል ሦስት

## የወሰን አከላለል ኮሚቴ አሰያየም እና የልዩ ልዩ አካላት ሥልጣንና ተግባር

### 10. የወሰን አከላለል ኮሚቴ አሰያየም

1/ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የከተማ አስተዳደር ከተሞችን ወሰን የሚከልል ከተለያዩ አካላት የተውጣጡ አባላት የያዘ ኮሚቴ በፕላን እና ልማት ቢሮ ይሰየማል፤

2/ የኮሚቴ አባላት ስብጥርም፡-

ሀ) የፕላንና ልማት ቢሮ ተወካይ/ ---------------------------------------------- ሰብሳቢ፣

ለ) ከተማ አስተዳደር ክንቲባ ጽሕፈት ቤት ---------------------------------------------- ፀሀፊ፣

ሐ) ወረዳ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ---------------------------------------------- አባል፣

መ) ወረዳ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት ---------------------------------------------- አባል፣

ሠ) የወረዳ መሬት ጽሕፈት ቤት ---------------------------------------------- አባል፣

ረ) የወረዳ ገቢዎች ጽሕፈት ቤት ---------------------------------------------- አባል፣

ሰ) የወረዳ ሰላምና ፀጥታ ጽሕፈት ቤት ---------------------------------------------- አባል፣

ሸ) የከተማ አስተዳደሩ ሰላምና ፀጥታ ጽሕፈት ቤት ---------------------------------------------- አባል፣

ቀ) የከተማ አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ---------------------------------------------- አባል፣

በ) ወደ ከተማ አስተዳደሩ የተካተቱ የገጠር ቀበሌ አስተዳዳሪዎች ---------------------------------------------- አባላት፣

ተ) የወረዳ ፕላን እና ልማት ተቋም ---------------------------------------------- አባል፣

ቸ) የከተማ አስተዳደር ፕላን እና ልማት ተቋም ---------------------------------------------- አባል፤

## 11. የኮሚቴው አሰራርና ኃላፊነት

ኮሚቴው የአስተዳደር ወሰን ሲሰራ፡-

1/ ቋሚ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ ምልክቶችን /መንገድ፣ ወንዝ፣ ተራሮች ወዘተ) እና በተጨማሪም ካርታዎች፣ ማዕዘን ድንጋይ እና የፅሁፍ መግለጫዎች መሠረት ያደርጋል፤

2/ የደረሰበትን ውጤት ቃለ ጉባኤ ይይዛል፣ በቃለ ጉባኤው ላይም ሁሉም የኮሚቴው አባል እንዲፈርሙ ያደርጋል፤

3/ የማጠቃለያ ሪፖርቱን በካርታ በማስደገፍ ለሚመለከተው ወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ያቀርባል።

## 12. ስለ ወሰን ማካለል ጉዳይ ቅሬታ ኮሚቴ እና የሚነሱ አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት ሁኔታ

1/ በወሰን ማካለል ጉዳይ በሪጅ-ፖሊታን፣ በመካከለኛ፣ በአነስተኛ ከተሞች እና በገጠር ወረዳዎች ወይም ወረዳዎች ከወረዳዎች፣ዞኖች ከዞኖች ጋር አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ወይም የይገባኛል ጥያቄዎች ሲነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት በየደረጃው የሚመለከታቸው የወሰን ማካለል ጉዳይ ቅሬታ ኮሚቴ የተነሱትን ጉዳዮች በማጥናት የሚመለከታቸውን አካላት በማወያየት እልባት የሚሰጥ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ ተደራጅቷል፤

2/ የወሰን ጉዳይ ቅሬታ ኮሚቴ ጉዳዩ በቀረበለት ሦስት ወር ጊዜ ውስጥ በማጠናቀቅ ውሳኔውን ለክልል ፕላን እና ልማት ቢሮ ማሳወቅ አለበት፤

3/ የወሰን ጉዳይ ቅሬታ ኮሚቴ አባላት ስብጥር የሚከተሉትን ያካተተ ይሆናል፡-

ሀ) ከፕላንና ልማት ቢሮ------------------------------------------------------ ሰብሳቢ፣

ለ) የዞን/ ወይም ወረዳ/ አስተዳዳሪዎች ----------------------------------------- ፀሀፊ፣

ሐ) የዞን ወይም ወረዳ አስተዳደር መሬት መምሪያ/ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ---------- አባል፣

መ) የዞን ወይም ወረዳ አስተዳደር የሠላምና ፀጥታ መምሪያ/ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች --- ------------------------------------------------------------------------------------------------------ አባል፣

ሠ) የዞን ወይም ወረዳ አስተዳደር የፖሊስ መምሪያ/ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎ ------- አባል፣

ረ) የዞን ወይም ወረዳ አስተዳደር ፕላን እና ልማት ተቋም --------------------- አባል፣

ሰ) የዞን ወይም ወረዳ አስተዳደር ፍትህ መምሪያ/ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች ---- አባል፣

ሸ) የዞን ወይም ወረዳ አስተዳደር ከተማና መሠረተ ልማት ጽሕፈት ቤት ------ አባል፣

ቀ) የወረዳ ገቢዎች ጽሕፈት ቤት --------------------------------------------------- አባል፣

በ) የከተማ የምህንድስና ባለሙያ ------------------------------------------------------- አባል፣

ተ) ችግሩ የተከሰተበት ቀበሌ አስተዳደር ሊቀመንበር ------------------------------ አባል፣

ቸ) ችግሩ በተከሰተባቸው ቀበሌዎች ውስጥ የሚገኙ የሀገር ሽማግሌዎች ሦስትነ -------- ------------------------------------------------------------------------------------------------ አባላት፤

ነ) ችግሩ በተከሰተበት ቀበሌ ውስጥ ተመድቦ የሚሰራ የመሬት ባለሙያ --------- አባል::

## 13. የኮሚቴው አሠራር እና ኃላፊነት

1/ በየደረጃው የተቋቋመው ኮሚቴ የተፈጠሩትን የወሰን ይገባኛል ጥያቄዎች በተዓማኒነት ያጠናል፤

2/ እውነተኛነት ያላቸውን ቋሚ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ ምልክቶችን ማለትም መንገድ፣ ወንዝ፣ ተራሮች... ወዘተ እና በተጨማሪም ካርታዎች፣ ማዕዘን ድንጋይ፣ የፅሁፍ መግለጫዎችን እንዲሁም እውነተኛ ናቸው የሚላቸውን ግለሰቦች በመረጃና ማስረጃነት ያደራጃል፤

3/ ባህላዊና ሳይንሳዊ የወሰን ግጭት አፈታት ዘዴዎችን በመቀመርና በመጠቀም ተግባራዊ ያደርጋል፤

4/ በሰበሰበው መረጃና ማስረጃ መሠረት የኮሚቴው አባላት በተገኙበት የውሳኔ ሀሳቡን በማያሻማ ሁኔታ በቃለ-ጉባኤ ይይዛል፣ በቃለ ጉባኤው ላይም ሁሉም የኮሚቴው አባላት እንዲፈርሙ ያደርጋል፣

5/ ኮሚቴው ማጠቃለያ ሪፖርቱን በካርታ እና በጽሁፍ ትንተና በማስደገፍ ለሚመለከተው ክልል/ዞን/ ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ያቀርባል።

## 14. በኮሚቴው ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ

ማንኛውም የአስተዳደር እርከን በኮሚቴው የወሰን አከላለል ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ ለክልሉ ፕላን እና ልማት ቢሮ የማቅረብ መብት ይኖረዋል።

## 15. ስለ ፕላን እና ልማት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

በዚህ መመሪያ ሌሎች ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ የፕላንና ልማት ቢሮ፡-

1/ የአስተዳደራዊ ወሰን ለማካለል የመምራት፣ የማስተባበር፣ አቅጣጫዎችን የማስቀመጥ፣ የመመሪያውን አተገባበር የመከታተል እና የመደገፍ ተግባራትን ያከናውናል፤

2/ እስከ ታችኛው የከተማና ወረዳ አስተዳደር እርከን ድረስ ስልጠናዎችን በመስጠት እንዲሁም ሌሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘዴዎችን በመጠቀም የከተሞች፣ የገጠር ወረዳዎችና ቀበሌ ባለሙያዎችን ግንዛቤ ያሳድጋል፤

3/ መመሪያውን ተግባራዊ በማያደርጉ የከተማ፣ የገጠር ወረዳና ቀበሌ አስተዳደሮች ላይ አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## 16. ስለ ከተሞች፣ ገጠር ወረዳዎች እና ቀበሌ አስተዳደሮች ተግባርና ኃላፊነት

1/ በማካለል ሂደት የከተማ አስተዳደር ማስተር ፕላን ከከተማው ወቅታዊ አስተዳደራዊ ወሰን አልፎ ሲገኝ በከተማው እና በገጠር ወረዳው መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶችን ለማስቀረት የከተማው ማስተር ፕላን ከመሰራቱ በፊት በዙሪያ የገጠር

ወረዳዎች ጋር በመነጋገር ቀጣይ ከተማው ሊያድግበት በሚችለው መልኩ በመወያየት ማሰራት ይኖርባቸዋል፤

2/ በዚህ መመሪያ የቅሬታ አፈታት ሥርዓትና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አለመግባባቶችን በራሳቸው የሚፈቱ ካልሆነ ከተማው እና የገጠር ወረዳው የሚገኝበት ዞን አስተዳደር ሁለቱን አካላት በማነጋገር እልባት መስጠት ይኖርበታል፤

3/ ማንኛውም የከተማ፣ የገጠር ወረዳ እና ቀበሌ አስተዳደር ይህን መመሪያ መነሻ በማድረግ፡-

ሀ) እንደ ተቋሙ ተጨባጭ ሁኔታ ማንዋል ሊያዘጋጅ ይችላል፤ ወይም እንዳለ በመውሰድ ሊጠቀም ይችላል፤

ለ) በሁሉም የአስተዳደር እርከንና የሥራ ክፍሎች ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሐ) እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ስልጠናዎችን በመስጠት እንዲሁም ሌሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘዴዎችን በመጠቀም ስለ ወሰን አከላለል ግንዛቤ ያሳድጋሉ።

4/ ማንኛውም የከተማ፣ የገጠር ወረዳ እና ቀበሌ አስተዳደር፡-

ሀ) ሕጋዊ የወሰን ማካለል ሥራዎችን በቅንነትና ታዓማኒነት የማስተባበር፣ የማስፈፀምና የመፈጸም ኃላፊነት አለበት፣

ለ) የወሰን ማካለል ተግባራት እንዲካሄዱ የሚተገበሩ ቅድመ-ዝግጅቶችን የማሟላት ኃላፊነት አለበት፣

ሐ) የወሰን ማካለል ሥራው በፕላን እና ልማት ባለሞያዎች ከተፈፀመ በኋላ ስጭና ተቀባይ አካላት ውሳኔውን ተቀብለው ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፣

መ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) ቢኖርም ለወሰን ማካለል ሥራው በመነሻነት የሚረዱ የቅድመ-ዝግጅት መረጃዎች ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፣

ሠ) መሟላት ያለባቸው ሕጋዊ አሠራሮች ከቅድመ-ወሰን ማካለሉ ሥራ ቀድመው መጠናቀቃቸው ተረጋግጦ የፕላን እና ልማት ባለሙያዎች ወደ ቦታዎቹ ሲሄዱ

እና ሥራቸውን ሲሰሩ በሂደቱ ባለሙያዎችን የማስተባበር እና የመደገፍ ኃላፊነት አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 17. ስለ መተባበር ግዴታ እና ተጠያቂነት

1/ ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ ሙሉ ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

2/ በየትኛውም የአስተዳደር እርከን አዋሳኝ ቀበሌዎችን በአሰራሩ መሠረት ለማካተትና ወሰናቸውን ለማካለል በሚያደርጉት ሕጋዊ ሂደት የሚካተቱትን ቀበሌዎች ለከተሞች ወይም ተገቢነቱ ለታመነበት የአስተዳደር እርከን ላለመስጠት የሚደረጉ ቢሮክራሲያዊ ውጣውረዶች የተከለከሉ ናቸው፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ይህን መመሪያ ተፈፃሚ በማያደርጉት አካላት ላይ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የባለጉዳዩ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይም የሚመለከተው አካል መረጃውን አደራጅቶ ለሚመለከተው የሕግ አካል በማቅረብ ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

### 18. ወሰንን ስለ ማሻሻል

የአንድ ከተማ ወይም የገጠር ወረዳ ወይም ቀበሌ ወሰን ሊሻሻል የሚችለው፡-

1/ አግባብ ያለው አካል የአስተዳደር እርከን ለውጥ ማድረጉ ሲረጋገጥ፤

2/ በከተማ ደረጃ ለውጥ እና ሽግግር ምክንያት ሲሻሻል፤

3/ በከተማው ዙሪያ የሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች በምክር ቤቶቻቸው አስወስነው ወደ ከተማ አስተዳደሩ የእንካተት ጥያቄዎችን አቅርበው አግባብ ባለው አካል ተቀባይነት ማግኘታቸው ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

## 19. መመሪያውን የማሻሻል ሥልጣን

የፕላን እና ልማት ቢሮ በጥናት ላይ ተመሥርቶ በሚያቀርበው የማሻሻያ ጥያቄ መሠረት መስተዳድር ምክር ቤቱ ሲያምንበት ይህንን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል።

## 20. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 21. `መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ ከታህሳስ 01/2018 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ ከመመሪያው ጋር በተያያዘ የሚነሳ መብትና ግዴታ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትሕ ቢሮ ተመዝግቦ በፕላንና ልማት ቢሮ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

**ባህር ዳር**

**ቀን 01/4/2018 ዓ.ም**

**ደመቀ ቦሩ ዶ/ር**

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕላንና ልማት ቢሮ ኃላፊ**